# ይድረስ፡-

## ለክቡራትና ለክቡራን፡ የጎዋ-ሰሌዳችን ታዳሚዎች!

"ኮነ ፍሥሓ ወሰላም! ደስታና ሰላም ኾነ!" በሚለው የምሥራች ቃል የሚጠቃለለውን፡ "የኢየሱስ መሲሕን፡ ከሙታን መካከል ተለይቶ የመነሣቱንና የማረጉን" የሰላምና የደስታ ሰላምታችንን እያስቀደምንላችሁ፡ ከዚህ በማስከተል፡ እነሆ፡ እንዲህ የሚል፡ መጠይቃዊ መልእክትን አቅርበንላችኋል።

ፈጣሪያችንና አምላካችን፣ መምህራችንና ሰላማችን፡ ወልደ-አብ ወወልደ-ማርያም፣ እግዚአብሔር ቃል፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ «"ምን ብለን እንደምንጸልይ አስተምረን?!" ብለው ለጠየቁት ደቀ-መዛሙርቱ፡ "እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ!" ብሎ ባስተማራቸው፣ "አቡነ ዘበሰማያት! የሰማያት አባታችን ሆይ!" በሚለው ጸሎቱ ውስጥ፡ <u>‹ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፣ ሀበነ ዮም! የየቀኑን መፍቅዳችንን [ነፍሳዊ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎታችንን]፡ ዛሬም ስጠን!›</u> በሉ!» የሚለው ቃሉ አለ።

በዚህ ረገድ ያለው፡ የእርሱ፡ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፣ የመምህራችንና የሰላማችን፡ የወልደ-አብ ወወልደ-ማርያም፣ የእግዚአብሔር ቃል፡ ኢየሱስ መሲሕ ስጦታ፡ "ነፍሳዊዉን፥ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን ፍላጎቶቻችንን ኹሉ፡ ያለልክ ያሟሉ፡ ግዙፍና ረቂቅ፣ እውንም የኾኑ ጸጋዎችንና በረከቶችን፡ በሥነ ፍጥረት፡ እንዲህ፡ ከመጠን በላይ አትረፍርፎ ያቀዳጀን መኾኑ፡ በገሃድ የታወቀ ኾኖ ሣለ፣ ነገር ግን፡ ይህን የመሰለው ስጦታው፡ በዚህ ፡ ወደእርሱ በምናደርገው፡ የጸሎታችን መመሪያው፡ "የዕለት ምግባችንን፡ ለዛሬ ስጠን!" በሚለው ቃሉ፡ <u>*ለምን፡ በአንዲት ቀን ብቻ፡*</u> እንዲህ ውሱን ኾኖ እንዲቀርብለት ፈቀደ?

ለዚህ መልእክታዊ ጥያቄ፡ ማብራሪያ መልስ የኾነውን፣ ከእርሱ፡ ከራሱ፡ ከፈጣሪያችንና ከአምላካችን፣ ከመምህራችንና ከሰላማችን፡ ከእግዚአብሔር ቃል፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የተሰጠውን ፍካሬ፡ ከዚህ የመልእክት ጽሑፍ ጋር፡ በጎዋ-ሰሌዳችን ላይ፡ ይፋ ወጥቶ በቀረበው፡ በ፲፮ኛው መለኮታዊ ዐዋጅ ውስጥ ሠፍሮ ከመመልከታችሁ በፊት፡ ይህንኑ ምንባባችሁን፡ እዚህ ላይ፡ ለጥቂት አፍታዎች አቁማችሁ፣

እስኪ! እያንዳንዳችሁ፡ ለዚያ፡ «"ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፣ ሀበነ ዮም! የየቀኑን ምግባችንን፡ ዛሬም ስጠን!"በሉ!» በማለት፡"<u>*ለምን፡ በአንዲት ቀን ብቻ፡*</u> እንዲህ ውሱን ኾኖ እንዲቀርብለት ፈቀደ?" ለሚለው ጥያቄ፡ የእየራሳችሁን መልስ፡ በቅድሚያ፡ በጽሑፍ ከትባችሁ፡ እዚያው፡ ለእየራሳችሁ አሳውቁ!

ከዚያ በኋላ፡ የጀመራችሁትን፡ ይህንኑ ምንባባችሁን ቀጥሉበትና፡ የእናንተን፡ የየግላችሁን መልስ፡ በ፲፮ኛው መለኮታዊ ዐዋጅ ውስጥ ሠፍሮ ከሚነበበው፡ መደምደሚያ ጋር አስተያዩት፣ አመዛዝኑትም።